# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net sh1@ttomar.net

ገ_ት-ድበ_20170827_ዐማርኛ

## የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የትንሣኤ ፡ እና ፡ የድል ፡ በዓል ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡–

# « ርትዕ ፡ እና ፡ መሥዋዕት ፥ የድል ፡ መሠረት ! »

ለንደን ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

እንኳን ፡ **ለጌታችን ፡ ለመድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የትንሣኤ ፡ በዓል ፡ እና ፡ ለሚያዝያ ፡ 27 ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ድል ፡ በዓል** ፡ በሰላም ፡ አደረሰኽ ፡ እያለ ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ ውጥን ፡ አካልኽ ፥ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት** ፡ ( **ኢ.ሀ.ሥ.አ.** ) ፡ መልካም ፡ ምኞቱን ፡ በትሕትና ፡ ያቀርብልኻል ።

የትንሣኤ ፡ በዓልን ፡ እና ፡ የድል ፡ በዓል ፡ 84ኛ ፡ ዓመትን ፡ በምናከብርበት ፡ ሰሞን ፥ በዠግኖች ፡ ልጆችኽ ፡ የፋኖ ፡ ንቅናቄ ፡ አባላት ፡ ተጋድሎ ፥ ዳግም ፡ የድል ፡ አድራጊነትን ፡ እና ፡ የሀገራዊ ፡ ድኅነትን ፡ መልእክት ፡ ከእየአግጣጫው ፡ እየሰማኽ ፥ የተስፋኽን ፡ ፍሬ ፡ ለማየት ፡ ትጠባበቃለኽ ። የጥቂቶቹ ፡ መሥዋዕት ፡ ሀገርን ፡ ያኽል ፡ ታላቅ ፡ እና ፡ ክቡር ፡ አለኝታን ፡ ስለ ፡ መታደጉ ፡ የሚያዝያ ፡ 27 ፡ ድል ፡ በዓል ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ማስታወሻው ፡ እና ፡ ማረጋገጫው ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፥ ጥቂቶች ፡ መሥዋዕትን ፡ ሲከፍሉልን ፥ ብዙኃኑ ፡ በተመልካችነት ፡ እና ፡ በተጠባባቂነት ፡ አረፍቀን ፡ የምንቈያቸው ፡ ቢኾን ፥ ሞት ፡ ይቀድመንና ፥ ከኹሉ ፡ ያጣን ፡ ኾነን ፡ እንቀራለን ።

ፋኖ ፡ የትጥቅ ፡ ትግሉን ፡ ትልም ፡ አሳይቶናል ፤ የትግሉን ፡ ፍሬ ፡ በጊዜ ፡ ለመረከብ ፡ ግን ፡ የመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተሳትፎ ፡ ግዴታ ፡ ይኾናል ። እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራውያን ፥ በእያለንበት ፥ እግዚእናችንን ፡ ወይም ፡ የሀገር ፡ ባለቤትነታችንን ፡ የምናረጋግጠው ፥ በምንገኝበት ፡ ጭቃ ፣ ቀበሌ ፣ ወረዳ ፣ አውራጃ ፣ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ እና ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያ ፥ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ በተባለው ፡ የውንብድና ፡ ይዘት ፡ መዳፍ ፡ ውስጥ ፡ የገቡትን ፡ የሀገር ፡ የመንግሥት ፡ እና ፡ የሕዝብ ፡ ተቋማትን ፡ እና ፡ ሕዋሳትን ፡ መልሰን ፡ እእጃችን ፡ አስገብተን ፥ ለፍትሕ ፡ እና ፡ ለርትዕ ፡ አስተዳደር ፡ የሚውሉበትን ፡ ኹኔታ ፡ ስናረጋግጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

የድል ፡ መሠረቱ ፡ ርትዕ ፡ እና ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ! የሕዝብን ፡ እግዚእና ፡ ለማስከበር ፡ የሚፈጸም ፡ ተጋድሎ ፥ ተኳድሎ ፡ የነበረን ፡ ርትዕ ፡ በመሥዋዕት ፡ በማሟላቱ ፡ በድል ፡ ይጸድቃል ።

በኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነት ፡ ( በዐምሐራነት ) ፡ በተደራጁ ፡ የቊርጥ ፡ ቀን ፡ ዠግኖች ፡ ልጆችኽ ፡ ፋኖዎች ፡ መሪነት ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ ለማስከበር ፡ የወጠንከውን ፡

ተጋድሎ ፡ በድል ፡ ለማጠናቀቅ ፡ ጥቂት ፡ ቀርቶኻል ። ይህ ፡ የተናጠል ፡ ተጋድሎ ፡ ግን ፡ ተሰናክሎም ፡ ተጠልፎም ፡ ድልኽን ፡ ሊያዘገይብኽም ፡ ሊያከሽፍብኽም ፡ ይችላልና ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ መሳውን ፡ ከትግሉ ፡ በባለቤትነት ፡ ሊሳተፍ ፡ ይገባዋል ።

ወደ ፡ ፊት ፡ በሚወሰን ፡ ቀነ ፡ ቀጠሮ ፥ በመሳ ፡ ኢትዮጵያ ፥ በእያንዳንዱ ፡ የገጠር ፡ እና ፡ የከተማ ፡ ቀበሌ ፥ በአንድ ፡ ቀን ፡ እና ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ በመነሣት ፥ መሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የእየአካባቢውን ፡ መንግሥታውያን ፡ ተቋማት ፡ እና ፡ ድርጅቶች ፡ በመቈጣጠር ፥ በመሳ ፡ ሀገርኽ ፡ ላይ ፡ እግዚእናኽን ፡ ለማረጋገጥ ፡ እንድትዘጋጅ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ( ኢ.ሀ.ሥ.አ. ) ፡ የሀገር ፡ ፍቅር ፡ ጥሪውን ፡ እንሆ ፡ በታላቅ ፡ አክብሮት ፡ ያስተላልፍልኻል ።

የትግልኽ ፡ ዐላማ ፦

- ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ ማስከበር ፥
- ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ መሥራት ፥
- ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥትኽን ፡ መመሥረት ፡

ስለ ፡ ኾነ ፦

" ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ ። "

( www.slttunhzb.net )

በተሠኘው ፡ ሰነድ ፡ ዝርዝር ፡ ክንዋኔው ፡ በኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ተደንግጎ ፡ ቀርቦልኻል ። ሰነዱን ፡ መክረኽበት ፡ ስትስማማበት ፡ እና ፡ በሥራ ፡ ስታውለው ፥ በቀናት ፡ ለድል ፡ እንደምትበቃበት ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ይተማመናል ፨

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፥

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ።

# እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥

# ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥

# ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

# ሥልጡንሕዝብና ።

# www.slttunhzb.net